# በውሸት ሕዝብን ማታለል አይቻልም!

## ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
## የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ. ም.
May 22, 2008

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ለሱዳን የተሰጠውን የሀገራችንን ለም መሬት በተመለከተ የሚፈጸመውን ድብቅ ሴራ እየተከታተለ ያጋለጠው በአሉባልታ ሳይሆን በእውነት ላይ የተመሠረቱ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ነው። በኢትዮጵያ ይዞታ ሥር የነበረ ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር ስፋቱ ከ30 እስከ 50 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ዘልቆ የገባ ለም መሬት ለሱዳን መሰጠቱን ሱዳን ውስጥ የሚገኙ የዜና አውታሮች ይፋ ያደረጉትን ዜናና የጉዳዩ ባለቤት የሆነው በድንበሩ ዙሪያ የሚኖረው ሕዝባችንን መረጃ የተመረኮዘ ነው። ይህ በአካባቢው የሚኖሩና በእርሻ ሥራ የተሠማሩ ወገኖቻችን ምስክርነትና ጩኸት በተለያዩ የዜና አውታሮች ተሰምቶ በተለያዩ ድኅረ ገጾችም ተመዝግቦ ይገኛል።

በአባቶቻችንና በእናቶቻችን ደም ለረጅም ዘመናት ተከብሮ የኖረው ውሀ ገብ ለም መሬት ለባዕድ አገር መሰጠትና በዚሁ አካባቢ የሚኖሩ ወገኖቻችን እሮሮና ጩኸት ያስቆጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት በየአለበት በተጠናከረ መልክ ተቃውሞውን በማሰማት ላይ ይገኛል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዝምታ እንደማያዋጣው የኋላ ኋላ የተገነዘበው ወያኔ/ኢሕአዴግ ግንቦት 3 ቀን 2000 ዓ. ም. "ደባ ራሱን፣ ሥለት ድጉሱን" እንዲሉ ኃላፊነት የጎደለውና በተለመደ ቅጥፈት የተሞላ፣ ከአንድ መንግሥት ነኝ ከሚል አካል የማይጠበቅ፣ እምነቱና ክህደቱ በአንድ አረፍተ ነገር ላይ የሚሻሙበት መግለጫ ለማውጣት ተገዷል።

"ውሸትና ቅራሪ ሽምጥጥ ነው" እንዲሉ

- የወያኔ/ኢሕአዴግ ቡድን ከሱዳን አቻዎቻቸው ጋር የወሰን ችካል ሲተክሉ እጅ ከፍንጅ መያዛቸው እየታወቀ፤
- 34 የሚሆኑ ወገኖቻችን በሱዳን ጦር ታፍሰው ተወስደው እስካሁንም በሱዳን እሥር ቤት እየማቀቁ (ስድስቱ የት እንደደረሱ አይታወቅም) የድረሱልኝ ድምፅ እያሰሙ በአለበት ጊዜና፤
- ገበሬዎችም የእርሻ ሠፈሮቻቸውና ሀብታቸው እንደተቃጠለባቸው አቤቱታ ለመላው ዓለም በሚያቀርቡበት በአሁኑ ወቅት በአንድ በኩል "ውል እያስፈጸምን ነው፤" በሌላ በኩል ደግሞ "ሁሉም አሉባልታ ነው" ብሎ ጮቤ መርገጥና አንድ ኢትዮጵያዊ ገበሬ ከይዞታው እንዳልተፈናቀለ አድርጎ መግለጫ ማውጣቱ የወያኔ/ኢሕአዴግ የቅጥፈት ባሕርይና የውሸት መጠን ድንበር የለሽ መሆኑን ነው የሚያስገነዝበው።

አልፎ ተርፎም በመግለጫው "እስከ ዛሬ ያልተቋጨውን ድንበር ተግባር የሚያካልል የድንበር ኮሚሽን አቋቁሞ ኮሚሽኑ የተለያዩ ጠቃሚ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል" ይላል።

በመጀመሪያ "የድንበር ኮሚሽን" መቋቋሙ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ዜና ነው። ሁለተኛ "ኮሚሽኑ" ያከናወናቸው ጠቃሚ ተግባራት የተባሉት ምንድን ናቸው?

- አፄ ቴዎድሮስ ተወልደው ያደጉበትንና በጉልምስናና በንጉሣዊ ዘመናቸው ኢትዮጵያዊነቱን አስከብረውለት የነበረውን መሬት ለሱዳን ማስረከብ፣
- አፄ ዮሐንስ አንገታቸውን የሰውለትንና በአጥንታቸው ድንበሩን የከለሉትን ቦታ እንደ ተቀሰፈው ጭንቅላታቸው ለሱዳን ገጸ በረከት ማስረከብ ነው?
- ሱዳኖች ለዘመናት የሚመኙትን የጓንግና የሸንፋ ወንዞችን ከነለም መሬቶቻቸው አዲስ የዘይት ባለሀብት ለሆነው መንግሥት መቸርቸር?
- የሱዳን መንግሥት ጦር ሠራዊት የኢትዮጵያን የግዛት ክልል ጥሶ እንዲገባና የወገኖቻችን ንብረት እንዲያወድም ፈቃድ መስጠት?

- ወራሪው የሱዳን ጦር ወገኖቻችንን አሥሮ እንደ ምርኮኛ ሲወስድ በአካባቢው የነበረው የአግአዚ ጦር ዝም ብሎ እንዲመለከት መመሪያ መስጠት?

ተቋቋመ የተባለው "የድንበር ኮሚሽን" ከላይ የተጠቀሱትን አስነዋሪ ተግባራት ሲያከናውን እንደ ቆየ እንጂ ሀገርንና ሕዝብን የሚጠቅም ሥራ እንዳልሠራ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ይገነዘባል።

## ውድ ኢትዮጵያዊያን ሆይ!

አሁን ወያኔ/ኢሕአዴግ ሳይወድ ደብቅ ሥራው አደባባይ ወጥቶበታል፤ ከዚህ የሚከተለው እርምጃው የጉዳዩን መልክ በመቀየር ከፍተኛ ውዥንብር መፍጠርና በድንበሩ አካባቢ የሚገኙ ወገኖቻችንን በበለጠ በማሸበር ተቃውሞውን ማዳፈን እንደሚሆን ግልፅ ነው።

ወደፊት ወያኔ/ኢሕአዴግ የክልሉ ኑዋሪ ናቸው የሚላቸው የራሱን ሰዎች በዜና አውታሮች በማቅረብ አንድም የተፈናቀለ፣ ንብረቱ የተዘረፈና የወደመበት፣ የተቃጠለበት ኢትዮጵያዊ የለም የሚል ሐሰታዊ መግለጫ በመደጋገም እንደሚያስደምጥ የሚጠበቅ ነው።

እነዚህንና የመሳሰሉ ሸፍጦችን ለማቀናጀትም ይሆናል መግለጫው በወጣ በማግስቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ካርቱም ከተማ ተንደርድረው ገብተው ለሱዳን ፕሬዚዳንት እጅ የነሱት።

## ውድ ወገኖች ሆይ!

የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ፣ መሬት እየጠበበ፣ ምርት እየቀነሰ በሔደበት በአሁኑ ዘመን ለትውልድ ደንታ የሌለው ወያኔ/ኢሕአዴግ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ለዘመናት ሊመግብ የሚችል ለም መሬት ለባዕድ ቀርሶ ሲሰጥ በቸልተኝነት ማለፉ የትውልድ ተወቃሽ መሆን ነው። ከዚህም በላይ የድንበሩ መገፋት ወደፊትም ስለሚቀጥል "ዳሩ ሲወሰድ መሀሉ ዳር ይሆናል" ነውና ማናቸውም ኢትዮጵያዊ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት … ወ. ዘ. ተ. ልዩነት ሳይፈጥር የሀገራችንን ሉዓላዊነትና አንድነት ለማስከበር እንድንነሣ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ጥሪውን ያቀርባል።

በሌላ በኩል ደግሞ ካለምንም ጥፋታቸው ያውም ዘመድ አዝማድ ወገን በማያገኛቸውና ስንቅ እንኳ ማቀበል በማይቻልበት ሁኔታ በግፍ የታሠሩት ወገኖቻችን ከሱዳን ወህኒ ቤት በአስቸኳይ ተለቀው ወደ ውድ ሀገራቸው እንዲመለሱ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ አጥብቆ ያሳስባል።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ሠራዊት ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የድንበር መደፈርን በዝምታ ማለፍ ስለማይገባ፤ የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ የኢትዮጵያ መደፈር ቆጭቶት እንዲነሣና የሀገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር ከሚታገለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆም ጥሪ እናቀርባለን።

በትናንቱ ዕለት ረቡዕ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ. ም. የወያኔ/ኢሕአዴግ ጠቅላይ ሚኒስትር ለፓርላማ ያቀረቡትን ክህደት በተመለከተ ተከታይ መግለጫ የምናወጣ መሆኑን በቅድሚያ እንገልጻለን።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት በልጆቿ ይከበራል!
ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
e-mail:- leethiopia@yahoo.com